**የሞንትጎመሪ ካውንቲ የምርጫ ቦርድ**
**ስለ 2020 ፕሬዝደንታዊ አጠቃላይ ምርጫ በተመለከተ ተደጋግመው የሚነሱ ጥያቄዎች**
*(ኦገስት 29፣ 2020 ላይ የተሻሻለ)*

**ጥ ፦ ስለ 2020 ፕሬዝደንታዊ አጠቃላይ ምርጫ ማወቅ የሚገባኝ ዋና ቁልፍ ነገሮች ምንድን ናቸው?**

- ኖቬምበር 3፣ 2020 የምርጫ መልዕክት "ራስዎን ይጠብቁ፣ ከቤት አይውጡ እና በፖስታ ይምረጡ" ነው ምክንያቱም ደግሞ በኮቪድ-19 ወረርሽኝ እና በመራጮች እና በምርጫ ላይ የሚሰሩ ሠራተኞች ላይ በሚያስከትለው ጉዳት የተነሳ ነው።

- በበፖስታ በፖስታ ይምረጡ ማመልከቻዎች ኦገስት 24 ቀን፣ 2020 ላይ ተልከው ነበር። የባሎት የምርጫ መስጫዎች ከሴምፕቴምበር 24፣ 2020 ጀምሮ ይላካሉ። **ልክ እንደ የመጀመሪያ ደረጃ ምርጫ ዓይነት ፣ የባሎት የምርጫ ወዲያውኑ አይላኩሎትም። በፖስታ የባሎት ድምጽ መስጫን መጠየቅ አለብዎት።** ማመልከቻውን ከሞሉ እና የእርስዎን የባሎት የምርጫ መስጫ ካገኙ በኋላ፣ መራጮች ልክ እንደ ተቀበሉት የባሎት ድምጽ መስጫቸውን ሞልተው ወዲያውኑ እንዲመልሱ ይበረታታሉ።

- በፖስታ ምርጫዎን ሞልተው የሚመልሱባቸው ሁለቱ ምርጥ መንገዶች ፥ ለእርስዎ የሚሰጥዎትን ቅድሚያ የተከፈለበትን የመመለሻ የፖስታ መላኪያ በመጠቀም፣ በዩናይትድ ስቴትስ ፖስታ አገልግሎት ) ደብዳቤ ውስጥ የምርጫ ድምጽዎን በማስገባት፣ ወይም የእርስዎ የተመላሽ ፓስታ እና ባሎትዎን ከታች ተጠቀሱት የካውንቲው ደብዳቤ መቀበያ ሳጥን አንዱ ላይ በማስገባት ነው።

- እባክዎን፣ (የባሎት) ድምጽ መስጫዎን ለመላክ እስከ መጨረሻው ደቂቃ ድረስ አይጠብቁ። የዩኤስ ፖስታ አገልግሎት ደብዳቤውን በጊዜ ማድረስ እንዲችል ከኦክቶበር (ጥቅምት) 27፣ 2020 ቀን ባልበለጠ ጊዜው ውስጥ ምርጫ ድምጽ የተሰጠባቸውን ባሎቶች በፓስታ በፖስታ እንዲልኩ በአጽንዖት ይጠየቃሉ። <u>የባሎት ድምጽ መስጫዎች በፖስታ የተላከበት ቀን ምልክት ከምርጫ ቀን፣ ኖቬምበር 3፣ 2020 ማለፍ የለባቸው።</u>

ቦርዱ ከአብዛኛዎቹ በአንዱ "በፖስታ ይምረጡ" የፓስታ መቀበያ ሳጥኖች ውስጥ የባሎት ምርጫ ጽምጾችን እንዲያስገቡ ያበረታታል። የግዛቱ የምርጫ ቦርድ ከኦክቶበር መጀመሪያ ጀምሮ ፓስታ መቀበያ ሳጥኖችን ይተክላል እና በምርጫ ቀን ላይ እስከ 8:00 p.m. ድረስ ክፍት ሆኖ ይቆያል። የመቀበያ ሳጥኖች በሁሉም የቅድሚያ ምርጫ እና የምርጫ ቀን ማዕከላት እንዲሁም በምርጫ ቦርድ ቢሮ እና የሮክቪል ከተማ አዳራሽ ፣ ውስጥ ይገኛሉ።

- ለ ለዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዝደንት ወይም በባሎት የምርጫ መስጫው ላይ ለሚገኙ የሜሪላንድ ሌሎች ቢሮዎች ድምጽ ለመስጠት መመዝገብ አለብዎት።

- ከታች እንደተጠቀሰው፣ ከኦክቶበር 26፣ 2020 እስከ ኖቬምበር 2፣ 2020 ቅድሚያ ምርጫ ይኖራል።

- ከታች እንደተጠቀሰው፣ ኖቬምበር 3 ቀን፣ 2020 የምርጫው ቀን ላይ የምርጫ ጣቢያዎች ይኖራሉ።

- ተመሳሳይ ቀን የመራጭ ምዝገባ በቅድሚያ ምርጫ እና በምርጫ ቀን ጣቢያዎች ላይ ይኖራሉ። በዚያኑ ቀን ለሚደረግ ምዝገባ የኗሪነት ማረጋገጫ መታወቂያ ያስፈልጋል።

**ጥ፦ የባሎት ድምጽ መስጫ መጠየቅ ያስፈልጋኛል?**

አዎ! የባሎት ድምጽ መስጫ መጠየቅ ያስፈልጎታል። የባሎት ድምጽ መስጫ አስቀድመው ላልጠየቁ በፖስታ ለእያንዳንዱ መራጮች በፖስታ ድምጽ መስጫ ማመልከቻ አገስት 24 ቀን ደብዳቤ ተልኳል።
አሁን እዚህ ላይ ማመልከት ይችላሉ፦
https://voterservices.elections.maryland.gov/onlinemailinrequest/InstructionsStep1

ቤታቸውን የቀየሩ ፣ ለጊዜው ከቤታቸው ርቀው የሚገኙ፣ ወይም አርብ፣ ሴፕቴምበር (መስከረም) 8 ቀን፣ 2020 በፖስታ  በፖስታ ድምጽ ይስጡ ማመልከቻ ያላገኙ መራጮች፣ የሜሪላንድ ግዛት የምርጫ ቦርድ የመራጭ መመልከቻ መሳሪያ (ቮተር ሉካፕ ቱል  መጎብኘት ወይም መረጃቸውን ለማረጋገጥ እና የባሎት ምርጫ ድምጽ ለመጠየቅ በ 77788 ላይ CHECK የሚል ጽሁፍ (ቴክስት) መላክ አለባቸው።

**ጥ፦ የእኔን የባሎት ድምጽ መስጫ የት ነው ?**

የእርስዎን የባሎት ድምጽ መስጫ በማመልከቻዎ ላይ ያሰፈሩት አድራሻ ላይ እንልክሎታለን። የእርስዎን የደብዳቤ አድራሻ ለማረጋገጥ፣የሜሪላንድ ምርጫ ቦርድን የመራጭ መመልከቻ መሳሪያ (ቮተር ሉካፕ ቱል )ይጎብኙ ወይም ወደ 77788 CHECK የሚል ጽሁፍ (ቴክስት) ይላኩ። የእርስዎን አድራሻ የቀየሩ ከሆነ፣ አዲስ የባሎት ድምጽ መስጫ እንልክሎታለን። እስከ ኦክቶበር 13፣ 2020 ድረስ አድራሻዎን ማስተካከል ይገባዎታል።

**ጥ፦ በፖስታ ውስጥ የእኔን የባሎት ድምጽ መስጫ ያላገኘሁኝ ከሆነስ?**

የእርስዎን  በፖስታ ድምጽ መስጫ ማመልከቻ አንዴ ከሞሉ በኋላ፣  በፖስታ ድምጽ መስጫ ማመልከቻውን ለመቀበል እና ለማሰናዳት ቢሮአችን እስከ 10 ቀናት ድረስ ሊወስድበት ይችላል።   ኦንላይን የማመልከቻ ሂደትን ለፖስታ ድምጽ መስጫ መጠቀም እርስዎ የጠቀሱት አድራሻ ላይ  የፖስታ ምርጫ ባሎት ድምጽ መስጫ ለማድረስ ብዙ ቀናትን ይወስዳል።  ከኦክቶበር 1 ቀን፣ 2020 በኋላ ከጠየቁት 10 ቀናት በኋላ የእርስዎን የባሎት ድምጽ መስጫ የማይቀበሉ ከሆነ፣ የሜሪላንድ ግዛት የምርጫ ቦርድ መራጭ መመልከቻ መሳሪያ(ቮተርስ ሉክአፕ ቱል ]ን ይጎብኙ ወይም 77788 ላይ CHECK በማለት ጽሁፍ መልዕክት ይላኩ እና ተተኪ የባሎት ድምጽ መስጫ ለመጠየቅ አገናኙን (ሊንክ) ላይ ይጫኑ።

**ጥ፦ ያልተገኘ የባሎት ድምጽ መስጫ ከዚህ ቀደም ጠይቄአለሁኝ። ሁለት የባሎት ድምጽ መስጫ ላገኝ እችላለሁኝ?**

አይ፣ የእርስዎ የምርጫ ምዝገባ ካልተቀየረ በስተቀር፣ ወይም ምትክ የባሎት ድምጽ መስጫ እንዲታተምልዎት ካልጠየቁ በስተቀር አንድ የባሎት ድምጽ መስጫ ብቻ ያገኛሉ።

**ጥ፦ ያልተገኘ የባሎት ድምጽ መስጫ እና በፖስታ  የፖስታ ባሎት ድምጽ መስጫ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?**

ምንም ልዩነት የላቸውም።

**ጥ፦ የእኔን የባሎት ድምጽ መስጫ ለመሙላት  ምን መጠቀም አለብኝ?**

ጥቁር ወይም ሰማያዊ እስክሪብቶ ቢጠቀሙ ይመከራል። እርሳስ፣ ማርከር ወይም ክራዮን አይጠቀሙ።

**ጥ፡- የምርጫ ድምጹን በፖስታ ባሎት መመለስ ላይ መከተል ያለብን አስፈላጊ ቅደም ተከተሎች ምንድን ናቸው?**

***ቃለ መሃላው ላይ በስምዎ መፈረም እና ምርጫ የተደረገበት የባሎት ድምጽ መስጫ መመለሺያ ፖስታ ጀርባ ላይ ፊርማዎን ቀን ማስፈርዎ*** አስፈላጊ ነው። *በፖስታው ላይ ብቻ ይፈርሙ፣ የባሎት ድምጽ መስጫው ላይ እንዳይፈርሙ።* የባሎት ድምጽ መስጫውን በጥቁር ወይም ሰማያዊ እስክቢርቶ ምልክት ያድርጉ። የሰጡት ድምጽ ተቀባይነት እንዲያገኝ የባሎት ድምጽ መስጫውን እስከ ጥቅምት (ኦክቶበር_) 27 ቀን፣ 2020 ድረስ በፖስታ ይላኩት ወይም እስከ ህዳር (ኖቬምበር) 3 ቀን፣ 2020 ከምሽቱ 8:00 ፒ.ኤምሰዓት ድረስ የደብዳቤ መቀበያ ሳጥን ውስጥ ይጨምሩት። ለምርጫ ቦርዱ ምርጫ የተደረገበት የባሎት ድምጽ መስጫ ፖስታ መልሰው በሚልኩበት ሰዓት የፖስታ መላኪያው ወጪ ቅድሚያ የተከፈለበት ነው። የድረገጽ የባሎት ድምጽ መስጫ በፖስታው የመላኪያ ክፍያ ያስፈልገዋል።

**ጥ፡- የእኔን የባሎት ድምጽ መስጫ እንዴት መመለስ እችላለሁኝ?**

መመሪያዎች ከእርስዎ በፖስታ ይምረጡ የባሎት ድምጽ መስጫዎ ጋር ይላካሉ። የመራጭ ቃለ መሀላን ከፈረሙበት እና ቀኑን ከጻፉበት በኋላ፣ የመመለሻ ፖስታው ውስጥ የባሎት ድምጽ መስጫውን ያስገቡት። በፖስታ ሳጥን ውስጥ በቀላሉ ማስገባት ይችላሉ። እስከ ጥቅምት (ኦክቶበር) 27 ቀን፣ 2020 ድረስ ተሞልቶ በፖስታ እንዲላኩ እናበረታታለን። ከዩኤስ ደብዳቤ የመመለሻ የባሎት ድምጽ መስጫ ፓስታ ጋር ወይም መቀበያ ሳጥን ውስጥ የእርስዎን ባሎት ድምጽ መስጫ እራስዎት የሚያስገቡ ከሆነ ምንም ዓይነት ክፍያ የለውም። የእርስዎን የባሎት ድምጽ መስጫ በኤሌክትሮኒክስ የጠየቁ ከሆነ እና የእርስዎን ዩኤስ ደብዳቤ ፓስታ በመጠቀም ለመመለስ ከመረጡ፣ የመላኪያ ክፍያ መክፈል አለብዎ።

የሚመርጡ ከሆነ፣ በጌትርስበርግ ሜሪላንድ 18753 ኖርዝ. ፍሬድሪክ ጎዳና ፣ ላይ የሚገኘው የሞንትጎመሪ ካውንቲ የምርጫ ቦርድ የ 24 ሰዓት መቀበያ ሳጥን መጠቀም ይችላሉ።

በተጨማሪ፣ መራጮች በፖስታ ቤት ወይም በመቀበያ ሳጥን በኩል የባሎት ድምጽ መስጫቸውን ልክ እንዳገኙት መልሰው እንዲልኩ በጥብቅ ይበረታታሉ። **የመቀበያ ሳጥኖች የቅድሚያ ምርጫ ጣቢያዎች ወይም የምርጫ ጣቢያ ቦታዎች ላይ እስካሁን ድረስ አልተተከሉም፣ በሚጫኑበት ጊዜ የቦታዎቹ ዝርዝር ይቀርባል።** አንድ ጊዜ ከተጫኑ በኋላ፣ መራጮች የባሎት ድምጽ መስጫቸውን በማንኛውም ጊዜ ላይ የመቀበያ ሳጥኖች ያሉበት ቦታ ላይ እስከ 8:00 p.m. ሰዓት ድረስ ኖቬምበር 3 ቀን፣ 2020 ላይ ማስገባት ይችላሉ።

**ጥ፡- የመረጥኩትን የባሎት ምርጫ ድምጽ ለመመለስ የመጨረሻውን ማብቂያ ቀን ነው?**

የዩኤስ ፓስታ አገልግሎት የሚመልሱ ከሆነ፣ ፓስታው ላይ ህዳር (ኖቬምበር) 3 ቀን፣ 2020 መላኪያ ቀን ምልክት ሊኖረው ይገባል። አይጠበቁ። የባሎት ድምጽ መስጫዎን የፖስታ ስርጭቱ ውስጥ ህዳር (ኖቬምበር ) 2 ወይም 3 ቀን መላክ ልክ እንደ ህዳር (ኖቬምበር) 4 ቀን፣ 2020 ላይ የፓስታ የተላከበት ቀን ተብሎ ሊፈረጅ ይችላል። ይሄ የተከሰተ ከሆነ፣ የእርስዎ የባሎት ድምጽ መስጫዎ ተቀባይነት አይኖረውም።

የባሎት ድምጽ መስጫዎን በጌትርስበርግ፣ ሜሪላንድ 18753 ኖርዝ. ፍሬድሪክ ጎዳና ላይ በሚገኘው የምርጫ ቦርዱ የመቀበያ ሳጥን፣ ወይም በቅድሚያ ምርጫ እና በምርጫ ጣቢያ ቦታዎች ላይ በተዘጋጁት ተጨማሪ መቀበያ ሳጥኖች ላይ ሞልተው ያስገቡ ከሆነ፣ ምርጫው ህዳር (ኖቬምበር) 3 ቀን፣ 2020 ከምሽቱ 8:00 ፒ.ኤ. ሰዓት ላይ ከመጠናቀቁ በፊት ሊያስገቡት ይገባል።

**ጥ፡- የ USPS መቀበያ ሳጥን ወይም ፖስታ ቤት የት ማግኘት እችላለሁኝ?**

በቅርብዎ የሚገኘው ፖስታ ቤት እዚህ ላይ ማግኘት ይችላሉ። ምንም የፖስታ ክፍያ አያስፈልግም።

**ጥ:- የእኔን የባሎት ድምጽ መስጫ እንዳገኛችሁት እንዴት አውቃለሁኝ?**

ስለ የእርስዎ የባሎት ድምጽ መስጫ ሁኔታ የሚመለከት መረጃ የሜሪላንድ ምርጫ ቦርድን የመራጭ መመልከቻ መሳሪያ (voter lookup tool) በመጠቀም ወይም ወደ 77788 CHECK የሚል ጽሁፍ በመላክ ይገኛል።

**ጥ:- ለ 2020 ፕሬዝደንታዊ አጠቃላይ ምርጫ የቅድሚያ ምርጫ ይኖራል?**

አዎ። ለ 2020 ፕሬዝደንታዊ አጠቃላይ ምርጫ የቅድሚያ ምርጫ ይኖራል። የቅድሚያ ምርጫው ሰዓቶች ከጥቅምት (ከኦክቶበር )26 ቀን፣ 2020 እስከ ህዳር (ኖቬምበር) 2 ቀን፣ 2020 ከ ጠዋቱ 7:00 ኤ.ኤም ጀምሮ እስከ ምሽቱ 8:00 ፒ.ኤም ድረስ ይከናወናል። አስራ አንዱ የቅድሚያ ምርጫ የሚሰጥባቸው ቦታዎች ከታች ተዘርዝረዋል:-

- በቦህረር ፓርክ አክቲቪቲ ሴንተር (Activity Center at Bohrer Park)
- ደማስከስ የማህበረሰብ ሪክሬሽን ማዕከል (Damascus Community Recreation Center)
- ኤግዝኩቲቭ ቢሮ ሕንፃ (Executive Office Building)
- ጀርመንታውን ኮሙኒቲ ሪክሬሽን ማዕከል (Germantown Community Recreation Center)
- ጄን ኢ፣ ላውቶን ኮምዩኒቲ ሪክሬሽን ማዕከል (Jane E. Lawton Community Recreation Center)
- ማርሊን ፕሬዝነር ኮምዩኒቲ ሪክሬሽን ማዕከል (Marilyn Praisner Community Recreation Center)
- ሚድ-ኮውንቲ ኮምዩኒቲ ሪክሬሽን ማዕከል (Mid-County Community Recreation Center)
- ፖቶማክ ኮምዩኒቲ ሪክሬሽን ማዕከል (Potomac Community Recreation Center)
- ሳንዲ ስፕሪንግ የበጎፈቃድ የእሳት መከላከያ ማዕከል (ዘ ቦልሩም) Sandy Spring Volunteer Fire Department (The Ballroom)
- ሲልቨር ስፕሪንግ ሲቪክ ህንፃ (Silver Spring Civic Building)
- ዊተን ላይብረሪ እና ኮምዩኒቲ ሪክሬሽን ማዕከል (Wheaton Library & Community Recreation Center)

**ጥ:- የተለመደው የምርጫ መምረጫ ቦታዬ ላይ መምረጥ እችላለሁኝ?**

አይ፣ በየሰፈሩ የሚገኙ የምርጫ መምረጫ ቦታዎች ተዘግተዋል ምክንያቱም በተለመደው መልኩ ምርጫ ማከናወን "የኮሮናቫይረስ ስርጭትን ማስተላለፍ ያስችላል፣ እና የሕዝብ ጤና፣ በጎነት እና ደህንነት ላይ አደጋ ያመጣል።" ተብሎ ተወስኗል።

ከዚህ ቀደም እንደተጠቀሰው፣ የኮቪድ_19 ማህበራዊ ስርጭትን ለመከላከል፣ ሁሉም መራጮችን በፖስታ ምርጫ ማመለከቻ ይላክላቸዋል። እባክዎን ማመልከቻውን ሞልተው መልሰው ይላኩ እና የባሎት ድምጽ መስጫ ቅድሚያ ከተከፈለበት ደብዳቤ ጋር ይላክሎታል።

**ጥ:- የምርጫ ቀን ላይ የት መምረጥ እችላለሁኝ?**

በአካል በመገናኘት የሚደረግ ምርጫ የተወሰነ ይሆናል እና በፖስታ መምረጥ ለማይችሉ መራጮች ብቻ የተዘጋጀ ነው። የምርጫ ቀን ላይ የሚመርጡ ከሆነ፣ ማንኛውም የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ወይም የተመረጡ ተጨማሪ ቦታዎች ላይ ባሉት ማንኛውም ሰባት የቅድሚያ ምርጫ ጣቢያዎች አንዱ ላይ መምረጥ ይችላሉ። የሚከተሉት ላይ መምረጥ ይችላሉ:-

➢ አልበርት አንስታይን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Albert Einstein High School)

- ቤተሳዳ-ቼቪ ቼዝ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Bethesda-Chevy Chase High School)
- ክላርክስበርግ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Clarksburg High School)
- ኮለኔል ዛዶክ ማግሩደር ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Colonel Zadok Magruder High School)
- ደማስከስ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Damascus High School)
- ጌትርስበርግ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Gaithersburg High School)
- ጀምስ ሁበርት ብሌክ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (James Hubert Blake High School)
- ጆኔፍ ኬኔዲ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (John F. Kennedy High School)
- ሞንትጎመሪ ብሌር ሁለተኛ ት/ቤት (Montgomery Blair High School)
- በሰሜን ቤተሳዳ የሚገኘው ሞንትጎመሪ ካውንቲ ኮንፈረንስ ማዕከል ማሪዮት (Marriott)
- ናንሲ ኤች. ዳሲክ ኖርዝ ፖትማክ ኮሚዩኒቲ መዝናኛ ማዕከል (Nancy H. Dacek North Potomac Community Recreation Center)
- ኖርዝዌስት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Northwest High School)
- ኖርዝውድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Northwood High School)
- ፓይንት ብራንች ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Paint Branch High School)
- ፖሊሲቪል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Poolesville High School)
- ኩዊንስ ኦርቻርድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Quince Orchard High School)
- ሪቻርድ ሞንትጎመሪ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Richard Montgomery High School)
- ሮክቪል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Rockville High School)
- ሴኔካ ቫሊ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Seneca Valley High School)
- ሼርውድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Sherwood High School)
- ስፕሪንግብሮክ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Springbrook High School)
- ቶማስ ኤስ. ዉቶን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Thomas S. Wootton High School)
- ዋልት ዊትማን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Walt Whitman High School)
- ዋልተር ጆንሰን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Walter Johnson High School)
- ዋትኪንስ ሚል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Watkins Mill High School)
- ዊተን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Wheaton High School)
- ዋይት ኦክ ኮሚዩኒቲ መዝናኛ ማዕከል (White Oak Community Recreation Center)
- ዊንስተን ቸርችል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Winston Churchill High School)

**ጥ፡- ከቤት ቅርብ የሆነ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ መምረጥ አለብኝ?**

አይ፣ የምርጫ ቀን ላይ ለመምረጥ ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የቅድሚያ የምርጫ ማዕከል፣ ወይም የናንሲ ኤች. ዳሲክ ኖርዝ ፖቶማክ የማህበረሰብ መዝናኛ ማዕከል ወይም ዋይት ኦክ የማህበረሰብ መዝናኛ ማዕከል ጋር መሄድ አለብዎ።

**ጥ፡- አካለስንኩል ስለሆንኩ በፖስታ መምረጥ ያዳግተኛል። ያሉኝ አማራጮች ምንድን ናቸው?**

ቤትዎ ውስጥ ሆነው መምረጥ የሚፈልጉ ከሆነ፣ በድረገጽ የሚላክ የባሎት ድምጽ መስጫ መጠየቅ አመቺ ሊሆንሎት ይችላል እና የእርስዎን የባሎት ድምጽ መስጫ ላይ ምልክት ለማድረግ የሚያግዙት የግዛቱን ምርጫ

ቦርድ ኦንላይን መሳሪያ መጠቀም ይችላሉ። መሳሪያው አካለስንኩልነት ያለባቸው ግልሰቦች ከሚገለገሉባቸው የተለመዱ ሶፍትዌሮች ጋር ተኳኅሃዳኝ ነው፣ እና ከዚህ መሳሪያ ጋር የራስዎን ድጋፍ ሰጪ መሳሪያ መጠቀም ይችላሉ።

በሌላ ግለሰብ እገዛ የሚሰጥዎት ከሆነ፣ እንዴት እንደሚመርጡ ጥቆማ ሊያደርጉልት አይገባም እና የእርስዎ ቀጣሪ ወይም የቢሮ ሠራተኛ ወይም የእርስዎ ማህበር ተወካይ መሆን የለባቸውም እና የድጋፍ ሰጪ ምስክር ወረቀት መፈረም እና ከእርስዎ የባሎት ድምጽ መስጫ አያይዘው ሊልኩት ይገባል።

የድምጽ ማዳመጫ እና የቁልፍፓድ፣ ከፍተኛ ማነፃጸሪያ፣ እና ከፍተኛ የህትመት ተግባራት እና መራጮች ምርጫ በግል እና ለብቻቸው መምረጥ የሚያስችሉ ሌሎች በልዩ ሁኔታ የተዘጋጅ ባህሪያቶች የተገጠመላቸው የድምጽ የባሎት ድምጽ መስጫ የሚያቀርቡ የቅድሚያ ምርጫ እና የምርጫ ቀን የምርጫ ጣቢያዎች ላይ የባሎት ድምጽ መስጫ ምልክት ማድረጊያ መሳሪያዎች ይገኛሉ።

በፖስታ መምረጥ የሚችሉ መራጮች ረጅም ሰልፎችን ለመቀነስ እና በአካል መምረጥ የሚገባቸውን ሰዎች ጤና እና ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል በፖስታ ምርጫ ላይ እንዲሳተፉ ይጠየቃሉ።

**ጥ፦ የመራጭ ምዝገባ ቅጾችን ለማተም እና ከመራጮች ጋር ለማጋራት የት ላገኛቸው እችላለሁኝ?**

የወረቀት የመራጭ ምዝገባ ቅጾች በ 18753 ኖርዝ. ፍሬድሪክ ጎዳና በጌይተርስበርግ ፍሬደሪክ ሜሪላንድ 20877 በሚገኘው የምርጫ ቦርድ ቢሮ ወይም የምርጫ ቦርድ ቢሮን በ 240-777-8500 ላይ በመደወል ያገኛሉ።

የወረቀት መራጭ ምዝገባ ማመልከቻዎች ኦንላይን ላይ በሚከተሉት ቋንቋዎች ጭምር ይገኛሉ፦

- እንግሊዘኛ
- ኢስፓኞል
- ባህላዊ ቻይንኛ
- የተቃለለ ቻይንኛ
- ኮሪያኛ

የመራጭ መዝገባቸውን እነዚህን ቅጾች በመጠቀም የተመዘገቡ ወይም ያዘመኑ መራጮች ምዝገባቸውን ለማረጋገጥ የመራጭ ማሳወቂያ ካርድ በፖስታ ላይ ይላክላቸዋል።

**ጥ፦ አድራሻዬን ወይም የፓርቲ ዝንባሌዬን ለመቀየር የመጨረሻው ቀን መቼ ነው?**

የመምረጫ ምዝገባ ለማድረግ፣ ወይም የእርስዎን የመኖሪያ ቤት አድራሻ ወይም የፓርቲ ዝንባሌ የመቀየሪያ የመጨረሻው ቀን እሮብ፣ ኦክቶበር 13 ቀን፣ 2020 ላይ ነው። የእርስዎን የመራጭ ምዝገባን ለማረጋገጥ፣ የሜሪላንድ ግዛት ምርጫ ቦርድን የመራጭ መመልከቻ መሳሪያ (voter lookup tool) ይጎብኙ ወይም ወደ 77788 CHECK የሚል ጽሁፍ ይላኩ።

**ጥ፦ የባሎት ምርጫ ድምጽ ለመጠየቅ የመጨረሻው ማብቂያ ቀን መቼ ነው?**

የእርስዎን የደብዳቤ አድራሻ፣ የሜሪላንድ ግዛት ምርጫ ቦርድን የመራጭ መመልከቻ መሳሪያ (voter lookup tool) (ቮተር ሉካፕ ቱል ) በመጎብኘት ወይም ወደ 77788 CHECK የሚል ጽሁፍ በመላክ ያረጋግጡ።

የባሎት ድምጽ መስጫ ለመጠየቅ የሚያስፈልጎት ከሆነ፣ የባሎት ድምጽ መስጫ በፖስታ የመጠየቂያ

የመጨረሻው ቀን ማክሰኞ፣ ጥቅመት (ኦክቶበር) 20፣ 2020 ነው።

ፕሪንተር ያለዎት ከሆነ እና የራስዎን የባሎት ድምጽ መስጫ በቤትዎ ውስጥ ለማተም አስፈላጊውን የፖስታ መላኪያ አቅራቢያዎ የሚገኝ ከሆነ እና በፖስታ ሊልኩት የሚፈልጉ ከሆነ፣ በድረገጽ የሚላክ የባሎት ድምጽ መስጫ የመጠየቂያ የመጨረሻው ቀን ማክሰኞ፣ ጥቅምት (ኦክቶበር) 20፣ 2020 ነው። በድረገጽ የሚላክ የባሎት ድምጽ መስጫ የሚጠይቁ ከሆነ፣ የራስዎን የባሎት

ድምጽ መስጫ ለማተም የመለያ መግቢያ እና የይለፍቃል ይቀበላሉ እና መልሰው ለመላክ የራስዎን የፖስታ መላኪያ መክፈል አለብዎ። የግዛቱ ምርጫ ቦርድ የሚያጋጥሞትን ችግሮች በ 800-222-VOTE ላይ ይፈታሉ።

**ጥ፦ የባሎት ድምጽ መስጫ ማመልከቻዎች የማይሳተፉ መራጮች ጋር በፖስታ አይላኩም። ለምንድን ነው? የእኔ የመራጭ ምዝገባ የማይሰራ ነው ብዬ ካሰብኩኝ ምን ማድረግ አለብኝ?**

ባሎት ድምጽ መስጫ ማመልከቻዎች የማይመርጡ መራጮች ጋር በፖስታ አይላኩም ምክንያቱም የተላከላቸው ደብዳቤ ተቀባይ ሳያገኝ ሲመለስ ጊዜ ወይም ከሌላ ግዛት እንደተዘዋወሩ ማሳወቂያ ሲደርሰን በሜሪላንድ ግዛት ውስጥ "የማይሳተፉ" በመባል መራጮች ይፈረጃሉ።

የእርስዎ የመራጭነት ምዝገባ የማይሳተፉ ምድብ ውስጥ ገብቷል ብለው የሚያሳቡ ከሆነ፣ የሜሪላንድ ግዛት ምርጫ ቦርድን [የመራጭ መመልከቻ መሳሪያ (voter lookup tool) (](#)ቮተር ሉካፕ ቱል ) ይጎብኙ ወይም 77788 ላይ CHECK ብለው መልዕክት ይላኩ እና አድራሻዎን ያረጋግጡ። የእርስዎ አድራሻ የተቀየረ ከሆነ፣ እባክዎን በፍጥነት ያስተካክሉት ። በተጨማሪ የባሎት ድምጽ መስጫ ላይ እዚህ ማመልከት ይችላሉ።
https://voterservices.elections.maryland.gov/onlinemailinrequest/InstructionsStep1

**ጥ፦ አንድ መራጭ የምርጫ ቦርድ ቢሮ፣ የደብዳቤ ሳጥን ወይም የመቀበያ ሳጥን ውስጥ ሌላ መራጭን በመወከል በፖስታ ምርጫ የተደረገበት እና የታሸገ የተመረጠ የባሎት ድምጽ መስጫ ተቀብሎ ማድረስ ይችላል?**

የሌሎችን መራጮች የመረጡበትን የባሎት ድምጽ መስጫ ከመሰብሰብ፣ በአካባቢው የሚገኝ የምርጫ ቦርድ ማድረስ፣ የባሎት ድምጽ መስጫ ሳጥን፣ ወይም የደብዳቤ ሳጥን ላይ ማስገባታቸውን የሚያግድ ምንም ዓይነት የፌደራል ወይም የግዛት ሕግ የለም። የግዛቱ ሕግ ለአንድ መራጭ የባሎት ድምጽ መስጫ የሚቀበል እና የሚያደርስ የውክልና ሂደት ፈጥሯል፣ ነገር ግን ይሄ የአሰራር ሂደት የተመረጡባቸውን የባሎት ድምጾችን ወደ ባሎት መመለሻ ቦታዎች ላይ ለመመለስ አይተገበርም። አንድ ሰው ሌላ ሰው የመረጠውን የባሎት ድምጽ መስጫ መልሶ ከማስገባት ለማገድ በሜሪላንድ አጠቃላይ ጉባኤ ላይ ውሳኔ ይጠይቃል።

**ጥ፦ የምርጫ-ቀን ላይ የቅድሚያ ምርጫ ወቅት ተመሳሳይ-ቀን ምዝገባ ይኖራል?**

አዎ። ሆኖም ግን፣ የመራጭ ምዝገባ የመጨረሻው ቀን ኦክቶበር 13 ቀን ነው፣ ቢሆንም ጥቂት መራጮች ተመሳሳይ-ቀን ምዝገባ ዕድል መጠቀም አለባቸው። ልክ እንደ የሕዝብ ጤና መጠበቅ ሂደት፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ምርጫ ቦርድ መራጮች ከምርጫ ቀን በፊት እንዲመዘገቡ ይጠይቃል ምክንያቱም የባሎት ምርጫ ድምጽዎን በፖስታ መቀበል እና መመለስ እንዲችሉ። ተመሳሳይ ቀን የመራጭ ምዝገባ ሁሉም ይቅድሚያ ምርጫ እና የምርጫ ቀን ጣቢያዎች ላይ ይኖራሉ።

**ጥ፦ የማታለል ድርጊቶችን ለመከላከል የምርጫ ቦርዱ ምን እያደረገ ነው?**

የምርጫ ቦርዱ ለሁሉም ምርጫ እንደምናከናውናቸው የማታለል ድርጊቶችን ለመከላከል ተመሳሳይ የመከላከያ እርምጃዎች እየወሰደን ነው። ሁሉም ስርዓቶች የተዘጋጁት እያንዳንዱ መራጭ አንድ የመምረጥ ዕድል እና አንድ የባሎት ድምጽ መስጫ ብቻ እንዲኖራቸው ነው። ማንኛውም የማታለል ድርጊትወይም ማስረጃ ከተገኘ ምርመራ ይደረግበታል እና ለፍርድ ይመራል። ማንኛውንም አይነት የማታለል

ሙከራ ያዩ ወይም የሰሙ ከሆነ; የአጠቃላይ አቃቤ ሕግ ቢሮን በ 410-575-6300 ያግኙ ወይም እንግሊዘኛ እስፓኞል 410-230-1712 ወይም 1-888-743-0023 ከክፍያ ነፃ በሜሪላንድ ውስጥ ወይም በ TDD 800.735-2258 ላይ በመደወል ያጋልጡ።

**ጥ፦ የኮምፒውተር ጠለፋን (ሃኪንግ)ድርጊቶችን ለመከላከል የምርጫ ቦርዱ ምን እያደረገ ነው?**

የምርጫ ቦርዱ ለእያንዳንዱ ምርጫ እንደምናከናውናቸው የሳይበር ደህንነት ተመሳሳይ የመከላከያ እርምጃዎች እየወሰድን ነው። ለባሎት ድምጽ መስጫ እና አላላክ ባህሪያቶችን ጨምሮ፣ የግዛቱ የምርጫ ቦርድ በመላው ግዛት የመራጭ ምዝገባ ስርዓት ደህንነት ማስጠበቅ ላይ ከፍተኛ የሆነ ወጪ አውጥቷል። ከምርጫ ቀን በኋላ ለብዙ ሳምንታት ያህል ምርጫው እውቅና አይሰጠውም ምክንያቱም የኦዲት ስራ ለማከናወን፣ ቅሬታዎችን ለመመርመር፣ እና እያንዳንዱ ብቁ የድምጽ ምርጫ እንደተቆጠረ ለማረጋገጥ።

**ጥ፦ የቅድመ ምርጫ ወቅት ወይም የምርጫ ቀን በምርጫ ማዕከል ለመስራት እንዴት መመዝገብ እችላለሁኝ?**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የምርጫ ቦርድ የኖቬምበር 3 ፕሬዝደንታዊ አጠቃላይ ምርጫን ለማከናወን ልክ እንደ የምርጫ ታዛቢዎች እንዲሰለጥኑ መራጮችን በመመልመል ላይ ይገኛል። በምርጫው ውስጥ ለመስራት እዚህ መመዝገብ ይችላሉ።

**ጥ.: እንደ የምርጫ ቀስቃሽ ሠራተኛ (ካናቫስ ወርከር) ለመስራት እንዴት መመዝገብ እችላለሁኝ?**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የምርጫ ቦርድ ምርጫዎችን በፖስታ በፖስታ የባሎት ድምጽ መስጫ እና ጊዜያዊ የባሎቶች ድምጽ መስጫ ለማስናዳት እንደ የምርጫ ቀስቃሽ ሠራተኛ እንዲሰሩ መራጮችን እየመለመለ ነው። ልክ እንደ ምርጫ ቀስቃሽ ሠራተኛ ለማገልገል እዚህ ላይ መመዝገብ ይችላሉ።

**ጥ፦ የእኔን የመራጭ ምዝገባ ካርድ ቅጂ ለመጠየቅ እንዴት እችላለሁኝ?**

ለመምረጥ የመራጭ ምዝገባ ካርድዎ አያስፈልጎትም። ሆኖም ግን፣ አንድ ለመጠየቅ የሚፈልጉ ከሆነ፣ የሜሪላንድ ምርጫ ቦርድን የመራጭ መመልከቻ መሳሪያ (voter lookup tool) (ቮተር ሉካፕ ቱል ) በመጠቀም ወይም ወደ 77788 CHECK የሚል ጽሁፍ በመላክ መጠየቅ ይችላሉ።

**ጥ፦ ለበለጠ መረጃ የት መሄድ እችላለሁኝ?**

ስለ ኖቬምበር 3 ቀን፣ 2020 ምርጫ ከሜሪላንድ ግዛት የምርጫ ቦርድስለፐሬዝደንታዊ ቀዳሚ ምርጫ በተመለከተ የወጣው መረጃ እዚህ ይገኛል። ከሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና ሰብዓዊ አገልግሎቶች መምሪያ ስለ COVID-19 ስለወጣው መረጃ እዚህ ላይ ይገኛል።

1. Reviewed by Yenehet Deggefa ,10/1/2020
2. Reviewed by Demeke Seyoum 10/01/2020